

## ☙ 11 ❧

# ሄሮዳውያን (ወላዋይ)

### 11-1

## የሄሮሳውያን ታሪክና አመጣጥ

ክርስቶስ በምድር በነበረበት ዘመን ስድስት ዓይነት እቅስቃሴዎች (ክፍሎች) እንደነበሩ ባለፉት ትምህርታችን ገልጸናል። እነርሱም ፈሪሳውያን፣ ሰዱቃውያን፣ ዜለትስ (ተቀናቃኞች) ኤኔሰንስ (አፈግፋጊዎች)፣ ሄሮዳውያንና ክርስትያኖች ናቸው። የመጀመሪያ አራቶቹን ባልፉት ትምህርቶቻችን ገልጸናቸዋል። በዛሬው ትምህርታችን የምናተኩረው ሄሮዳውያን (ወላውያን) እየተባሉ ይጠሩ በነበሩት ክፍሎች ላይ ይሆናል። በወንጌሎቹ ውስጥ ስለእነዚህ ክፍሎች በግልጽ የተዘረዘር ታሪክ የለም። ይህ ፓርቲ (ቡድን) የተቋቋመው በዘመኑ በስልጣን ላይ ለነበረው ለታላቁ ሄሮድስ ድጋፋቸውን በሚያሳዩ ሰዎች ነው። በሰላም ለመኖር በሥልጣን ላይ ላለው መገዛትና መስሎ መኖር፥ ተፈላጊውን ቀረጥ ለሮማ መንግሥት መክፈል አግባብ ነው ብለው የሚደግፉና የሚያምኑ ናቸው። እነዚህ ክፍሎች በአቋማቸው ከዜለትስ (ተቀናቃኞች) ማለትም የሮማን ቀንበር በጦርና በኃይል ለመስበር ከሚታገሉት ፍጹ የተቃረነ ሀሳብና አቋም ያላቸው ናቸው።

## የሄሮዳውያን አቋም

ሄሮዳውያን ያለውን የአገዛዝ ስርዓት ኢየሱስ ይለውጥብናል ብለው ይፈሩ ስለነበረ፥ ከፈሪሳ ውያን ጋር በመተባበር ሊያጠቁትና ሊያጠፉት ይሞክሩ ነበር። "…እንዴት አድርገው እንዲያጠፉት ከሄሮድስ ወገን ጋር ተማከሩበት" (ማር. 3፥6) "…በንግግርም ሊያጠምዱት ከፈሪሳውያንና የሄሮድስ ወገን የሆኑትን ወደ እርሱ ላኩ" (ማር. 12፥13)። ታሪኩን በቅጡ ለማታውቁ ኢየሱስ ከምድር በነበረበት ዘመን የአይሁድ ሕዝብ በሮም ግዛት ሥር ተጨቁነው ይኖሩ ነበር። መሲሁንም በናፍቆት ይጠብቁበት የነበረው ዋናው ምክንያት በጊዜ ከነበረባቸው ምድራዊ ጭቆና ነጻ ያወጣናል ብለው ገምተው ስለነበረ ነው። ሆኖም የኢየሱስ ግዛት በምድር ሳይሆን በሰማይ መሆኑን ሲገልጽላቸው እውነተኛ መሲህነቱን መቀበል አቃታቸው። ሄሮዳውያን በሄሮድስ አገዛዝ ሥር ተመችቶአቸው ስለ ነበር፥ ምቾታችን ይለወጥብናል ብለው ስለፈሩ የለወጡ ምክንያት ክርስቶስ ይሆናል ብለው ስለገመቱ አጥብቀው ይቃወሙት ነበር። ክርስቶስ የጋራ ጠላታቸው በመሆኑ እርሱን ለመቃወም ህብረት ይፍጠሩ እንጂ፥ ሄሮዳውያን ከፈሪሳውያን ጋር በእምነታቸውና በአጠቃላይ አቋማቸው አይቀራ ረቡም። ሄሮዳውያን ከፖለቲካ ፓርቲነት ከፍ ያለ፥ ከሃይማኖት ክፍል (ሴክት) ያነሰ አቋም ያላቸው ናቸው።

በዘመኑ የነበረው የኑሮ ችግር አንዳንዶቹን እለታዊ የኑሮ ችግራቸውን የሚያቃልሉበት ልዩ ልዩ መንገድ እንዲፈልጉ አድርጎአቸዋል። ከነዚህም ውስጥ አንደኛው በሥልጣን ላይ ሆኖ ከሚያስተዳ ድረው ገዥ ጋር ተስማምቶ የመኖር ዘዴ ነው። ሄሮድስ በዚያን ዘመን በስልጣን ላይ ስለነበረ ከእርሱ ጋር መልካም ግንኙነት ለመፍጠር ሞክረዋል። አይሁድ ሆነው የሮማ መንግሥት ተወካይ ሆኖ ለሚገዛ

ሄሮድስ ድጋፍ በመስጠታቸው "የሄሮድስ ሰዎች" የሚል ቅጽል ስም ተሰጥቶአቸዋል። እነዚህ ክፍሎች ሰላማ ቸውና የአኗኗር ሁኔታቸው እንዳይዛባ ሲሉ ብቻ "እሺ" ወይም "አሜን" ብለው ተቀብለው የሚኖሩ ናቸው።

## የዘመኑ ሄሮድውያን

ሄሮድውያን (የሄሮድስ ሰዎች) ጥንት ብቻ ሳይሆን በዘመናችንም በእምነት አቋማቸው እነርሱን የሚመስሉ አሉ። እነዚህም በባህሪያቸው ወላዋዮች ወይንም ዥንጉርጉሮች ናቸው። የሚፈልጉትን ለማግኘት ብቻ ሲሉ የማይወዱትን ያደርጋሉ። "ሁሉንም ማስደሰት" አለብን የሚል ባህሪ አላቸው። ከሚ ነፍሰው ጋር አብረው ይነፍሳሉ። ከሌሎች ሰዎች የተለዩ ሆነው መታየት አይፈልጉም። የራሳቸው የሆነ መመሪያ (ፕሪንስፐል) ስለሌላቸው ወደገፉዋቸው ይገፋሉ፤ ወደ ጠመዘዙዋቸው ይጠመዘዛሉ። በቀላሉ የሚወናበዱ ናቸው።

## እውነተኛ አማኝ እምነቱን አይደብቅም

ሐማ፥ ንጉሥ አርጤክስስ ከፍ ከፍ ያደረገውና፥ ያከበረው ሰው ነበር (አስቴር 3፥1)። ንጉሥ ትልቅ ላደረገው ይህንኑ ሐማ የንጉሥ ባሪያዎቹ ሁሉ ይሰግዱለት ነበር። "መርዶክዮስ ግን አልተደፋም፤ አልሰገደለትም" (አስቴር 3፥3)። መርዶክዮስ በአይሁድ እምነቱ መስገድ ያለበት ለእግዚአብሔር እንጂ ለተፈጠረው እንዳልሆነ ስለሚያውቅ ነበር። የመርዶክዮስ እምቢተኛነት እርሱን ብቻ ሳይሆን የአይሁ ድንም ዘር የሚያስጨርስ ቢሆንም፥ እምነቱን ደብቆ ለሃም መጎንበስን አልመረጠም። ለአይሁድ ሕዝ ብም መዳኛ እንዲሆን እግዚአብሔር የራሱን መንገድ እንደሚያዘጋጅላቸው በፍጹም ልቡ ያምን ነበር። ስለሆነም እስከ መጨረሻው ድረስ ልቡን ለአምላኩ እንጂ ለሰው አላስገዛም። "ይሄ ግትርነት ነው ምን አለ ቢሰግድለት? ከአደጋ ለማምለጥ በዘዴ ማለፉ ጥቅም አለው" የሚል አስተያየት መሠንዘሩ አይቀርም። ይሁን እንጂ መርዶክዮስ "ያለመናወጥ ተቀምጦ" (5፥9) ነበር። ክርስትያን ከስደት፣ ከችግር፣ ከመከራ ለማምለጥ ሲል ብቻ አምላኩን አይደብቅም። እምነቱን በሚመለከት ጉዳይ ላይ አያወላው ልም፤ አያመነታም።

## እውነተኛ አማኝ አያወላውልም

እምነታቸውንና አምላካቸውን በሚነካ አቅጣጫ ላይ አንገታችን አይታጠፍም ያሉ መንፈሳዊ አባቶ ቻችን ታሪክ ትተውልን አልፈዋል። ለዚህም ዋጋ ከፍለውበታል። መታሰር፣ መገረፍ፣ ሲበዛም መታረድ ደርሶባቸዋል። ከእነርሱም መካከል ሲድራቅ፣ ሚሳቅና አብድናጎ ይገኙበታል። እነርሱም "ናቡከደናጾር ለቆመው ምስል አንሰግድም" አሉ (ዳን. 3፥12) በማለት ለንጉሡ አስታወቁ።
በወቅቱ የተሰበሰበው ሕዝብ ለምስሉ ሲሰግዱ እነዚህ ሦስት ሰዎች ብቻ ተለይተው ቀጥ ብለው ቆሙ። እንቢተኛነታቸው ከአደጋ ላይ እንደሚጥላቸው ንጉሱ ለመጨረሻ ጊዜ አስጠንቀቃቸው። የሰጡት መልስ **"ናቡከደናጾር ሆይ! በእዚህ ነገር እንመልስልህ ዘንድ አስፈላጊ አይደለም። የምናመልከው አምላካችን ከሚነደው ከእሳቱ እቶን ያድነን ዘንድ ይችላል፤ ባያድነን እንኳን አማልክትህን እንዳናመልክ ላቆም ከውም ለወርቁ ምስል እንደማንሰግድለት እወቅ"** የሚል ነበር (ዳን. 3፥16-18)። እነዚህን ዕብራውያንን የሚነደው እሳት አላስፈራቸውምጎ ሞትም ቢሆን ያንን ለመቀበል ወስነው ስለነበር ፍርሃትና መወላወል አልታየ ባቸውም። ሐዋርያው ጳውሎስ በመንፈሳዊ ጉዞው ላይ ብዙ ችግር፣ ፈተናና ግፊት ደርሶበታል። ይሁን እንጂ በእምነቱ አንድ ጊዜም ወደኋላ አላለም። ሁለት ዓይነት ወይንም ዥንጉርጉር ሕይወት አልኖረም። ቆራጥ የሆነ ውሳኔውን ሲናገር፥ **"ከክርስቶስ ፍቅር ማን ይለየናል? መከራ ወይስ ጭንቀት፣ ወይስ ስደት፣ ወይስ ራብ፣ ወይስ ራቁትነት፣ ወይስ ፍርሃት ወይስ ሰይፍ ነውን?"** (ሮሜ 8፥35) አለ። እውነተኛ አማኝ

ስለእምነቱ ሲል እስከመታረድ ድረስ ይደርሳል እንጂ ፈጽሞ አያወላውልም። ሰላም ለማግኘት ብቻ እንደ ሄሮዳውያን ተስማምቶ እምነቱን ሸፍኖ አይኖርም። ሞትም ቢያስከትል የእምነት ባንዲራውን በግልጽ ከማውለብለብ ወደኋላ አይልም።

## ለዓለም አይሰግድም

ዲያብሎስ ኢየሱስን እጅግ ረጅም ተራራ ላይ ወስዶ የዓለምን መንግሥታት ሁሉ ክብራቸውን ካሳየው በኋላ “ወድቀህ ብትሰግድልኝ ይህን ሁሉ እሰጥሃለሁ” አለው (ማቴ. 4፥8-9)። ኢየሱስም ሐሳቡን በመቃወም ገሰጸው። ዲያብሎስ ለዚህ ዓለም ክብር እንዲንበረከክ ኢየሱስን እንኳን ከፈተነ፥ ተራ አማኝን እማ ምን ያህል ይፈትነው? የዓለም ክብርና ውበቷ ያጓጓል። ዘላቂነት የሌላት መሆኑን የተረዳ አማኝ ግን ለዓለም አይሰግድም። **“ሙሴ ካደገ በኋላ የፈርዖን የልጅ ልጅ እንዳይባል በእምነት እምቢ አለ። ከግብጽም ብዙ ገንዘብ ይልቅ ስለክርስቶስ መነቀፍ እጅግ የሚበልጥ ባለጠግነት እንዲሆን አስቦአልና ለጊዜው በኃጢአት ከሚገኝ ደስታ ይልቅ ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር መከራ መቀበልን መረጠ፤ ብድራቱን ትኩር ብሎ ተመልክቶአልና”** ይላል ዕብራውያን 11፥24-26።

ክርስትያን ለብልጽግና ልቡን ለምን እንደማይሰጥ ምክንያቱ ከላይ በግልጽ ተገልጿል። ይኸውም፥
1. ከዓለም ብልጽግና በክርስቶስ ውስጥ ሆኖ መወረዱ ይሻላል፤
2. የዓለም ደስታው ጊዜያዊ ነው፤
3. በኃጢአት ከሚገኝ ደስታ ይልቅ በቅድስና ኖሮ መሰቃየቱ የተሻለ ነው፤
4. በቅድስና መኖር ወደፊት ዋጋ አለው።

በዚህ ምክንያት ክርስትያን ከዓለም ጋር መስሎ ለመኖር ፍጹም ውሳኔ አያደርግም።

**የጌታ ጸጋና ሰላም ከእናንተ ጋር ይሁን። አሜን!**